# የቀጥታ ዘር ግብይት አተገባበር መመሪያ

የካቲት 2007 | ቢሾፍቱ

ግብርና ሚኒስቴር
Ministry of Agriculture
MoA

Ethiopian ATA
Agricultural Transformation Agency
የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ

## ማውጫ


መግቢያ ..... 2

1. የነባሩ ዘር ግብይት ስርዓት ..... 3

ሀ. የነባሩ ዘር ግብይት ስርዓት መገለጫ ..... 3

ለ. የነባሩ የዘር ግብይት ስርዓት ዋና ዋና ተግዳሮቶች ..... 3

ሐ. መልካም አጋጣሚዎችና ስልታዊ መፍትሄዎች ..... 3

2. የቀጥታ የዘር ግብይት ለምን አስፈለገ ? ..... 4

ሀ. የቀጥታ የዘር ግብይት እና ተያያዝ ቃላት ትርጓሜ ..... 4

ለ. የቀጥታ የዘር ግብይት ስርአት ዋና ዋና አላማዎች ..... 4

ሐ. የቀጥታ የዘር ግብይት ስርአት መርሆዎች ..... 5

መ. የቀጥታ የዘር ግብይት ዋና ዋና ፋይዳዎች ..... 5

ሠ. ያጋጠሙ የአፈጻጸም ተግዳሮቶችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች ..... 6

3. የቀጥታ ዝር ግብይት ሂደት ..... 7

4. የባለድርሻ አካለት የስራ ድርሻና ሃላፊነት ..... 7

ሀ. የዘር አምራች ድርጅት ..... 7

ለ. የሽያጭ ወኪሎች ..... 8

ሐ. የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ተቋም (ፌዴራል እና ክልል) ..... 8

መ. ግብርና ሚኒስቴር ..... 8

ሠ. የክልል ግብርና ቢሮ ..... 9

ረ. የሕብረት ስራ ማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ቢሮ/ኤጀንሲ/ፅ/ቤት ..... 9

ሰ. የክልል የዘር አብይ ኮሚቴ ..... 9

ሸ. የዞን ግብርና መምሪያ ..... 9

ቀ. የወረዳ ግብርና ጽ/ቤት ..... 10

በ. የቀበሌ ግብርና የልማት ጽ/ቤት ..... 10

ተ. የልማት አጋር አካላት ..... 10

ቸ. አርሶ አደሮች ..... 11

5. የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ..... 11

ሀ. ዋና የአፈጻጸም ጠቋሚ መለኪያዎች ..... 11

ለ. የክትትልና የግምገማ ግንኙነት ሂደቶች ..... 11

## መግቢያ

መንግስት ግብርናን ማዕከል ያደረገ የእንደስትሪ እድገት ፖሊሲ ነድፎ በመንቀሳቀስ ምርትና ምርታማነትን በዘለቄታዊ መንገድ ለማሻሻል ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ይገኛል:: ይህንንም ለማሳካት ከፍተኛ አስተዋጻኦ ያላቸውን የተሻሻሉ የግብርና ግባቶችን (ምርጥ ዝር፣ ማዳበርያ፣ ጸረ አረም ወዘተ…) በተፈለገው መጠን፣ ጥራት፣ አይነትና በተመጣጣኝ ዋጋ ለተጠቃሚው ማድረስ ወሳኝ ነው::

የምርጥ ዘርንም በተመለከተ የነባሩ ግብይት አሰራሮች ላይ የሚታዩ ተግዳሮቶችን መፍታት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቶል:: በዚህም መሰረት የቀጥታ የዘረ ግብይት ስረአት ተነድፎ ላልፉት አራት አመታት በተመርጡ የሙከራ ወረዳዎች በአራቱ ክልሎች (ደቡብ ህዝቦች፣ ትግራይ፣አማራ እና ኦሮሚያ ክልል) ሲተገበር ቆይቶል:: በአዲሱ የዘር የግብይት ስረአት የዘር አምራች ድርጅቶች ቀጥተኛ የሆነ ሃላፊነት ያላቸው ሲሆን የሚያምርቱትንም ዘር እውቅና ባላቸው የሽያጭ ወኪሎች በኩል ያከናውናሉ::

እስካሁን የተደረጉ የአፈጻጸም ግምገማ ውጤቶች እንደሚያመልከቱት አዲሱ የግብይት አሰራር ዘርን በውቅቱ፣ በበቂ ምጠን፣ በተመጣጣኝ ዋጋ ለተጠቃሚው እንዲቀርብ በማስቻል በኩል አበረታታች ወጤቶችን አስገኝቶል:: በነዚህ ውጤቶች ላይ በመመስረት በየአምቱ የማስፋት ስራ በመስራት ተጨማሪ አዳዲስ አክባቢዎች ላይ ዕንዲተገብር በግብርና ሚኒስተርና በክልል ግብርና ቢሮዎች አቅጣጫ ተቀምጧል::

ይህም የዘር ግብይት ስርዓት አዲስ አሰራር ከመሆኑ አንጻር የተለያዩ የግንዛቤ ክፍተቶች እንዳጋጠሙ መረዳት ተችሎል:: ስለሆነም የቀጥታ ይዘር ግብይት ስረአትን በአገር አቀፍ ደርጃ ወጥነት ባልው መልኩ እንዲትግበር ለማስቻል ይህንን የአተገባበር መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተግኝቶአል::

ይህ የዘር ግብይት መመሪያ የተዘጋጀው በየደረጃው ላሉ የክልል፣ የዞን፣ የወረዳ ፣የቀበሌ ባለሙያዎች፣ ፣ ዘር አምራች ድርጅቶች ፣ የዘር ሽያጭ ወኪሎች ፣ የዘር ተጠቃሚዎች እና ሌሎች አጋር አካላት ሲሆን አላማውም የቀጥታ ዘር ግብይት አፈጻጸም ላይ ያላቸውን የክህሎት ፣ የእውቀት እና የአመለካከት ክፍተት ለመሙላት ነው፡፡ በተጨማሪም ሁሉም ባለድርሻ አካላት የስራ ድርሻቸውን እና ሃላፊነታቸውን ለይተው እንዲያዉቁ እና ስርአቱን በባለቤነት ወስደው በመደበኛ እቅዳቸው ውስጥ በማካተት በዘላቂነት እንዲፈጻም ለማስቻል ነው፡፡

# 1. የነባሩ ዘር ግብይት ስርዓት

## ሀ. የነባሩ ዘር ግብይት ስርዓት መገለጫ

የሰብል ምርት ˆ ና ምርትማነትን ትርጉም ባለው ደረጃ ለማሳደግ የተለያዩ የግብርና ግብአቶችንና ተክኖሎጂች ጥቅም ላይ ˆ የዋሉ ይገኛሉ:: በዚህም ረገድ የአንበሳውን ድርሻ የሚወስደው የምርጥ ዘር መሆኑ ይq መናል::

ከጊዜ ወደጊዜ ˆ የጨመረ የመጣውን የአርሶአደሩን የምርጥ ዘር ፍላጐት በተገቢው ሁኔq ለማርካት ቁጥራቸው በርካq የሆኑ ድርጅቶች &ማህበራት ˆ ና የግል ባለሀብቶች አቅርቦትን በመጨመር በኩል ከፍተኛ ስራ ˆ የሰሩ ይገኛሉ::

ነገር ግን ˆ ነዚህ ድርጅቶች የዘር ግብይት ˆ ና ስርጭት ላይ ያላቸው ሚና ˆ ጅጉን ውስን ሆኖ ቆይቷል:: ይህንን ሀላፊነት በዋናነት በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የመንግስት አንካላት ተሸክመው ስርጭቱን ኮq ን መሰረት ባደረገ መልኩ በዩኒየኖች ˆ ና በመሰረq ዊ ሕብረት ስራ ማህበራት በኩል ብቻ ሲያከናውኑ ቆይተል:: ይህም ረጅም የሆነ የዘር አቅርቦት ሰንሰለት በመፍጠር ዘር በሚፈለገው መጠን &አይነት &ጊዜ ˆ ና ተጠያቂነት ባለው መልኩ ለተጠቃሚው ˆ ንዳይደርስ የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል:: በተጨማሪም ተጠቃሚው አርሶ አደር ከማህበራት ውጪ ዘርን ከአማራጭ አንካላት የማግኘት ˆ ድሉን ውስን አድርጐት ቆይቷል::

በሌላ በኩል አምራች ድርጅቶች ከደንበኞቻቸው ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ስላልነበራቸው ተገቢውን ግበረ መልስ ˆ ንዳያገኙና ˆ ርምት ˆ ንዳይወስዱ ሲያደርግ ቆይቷል:: በዚህም ምክንያት በዘር ፍላጐት ˆ ና አቅርቦት መንከል ከፍተኛ ልዩነት ሲq ይ ቆይቷል:: ከዚህም ጋር ተያይዞ በየአመቱ ከፍተኛ መጠን ያለው ዘር በማህበራት ˆ ንዲያድር ˆ ና ብሎም ለብክነት ˆ ና ለጥራት መጓደል ˆ ንዲዳርግ ምክንያት ሆኗል::

በአጠቃላይ መንግስት ከዘር ስርጭት ˆ ና ግብይቱ ጋር በተያያዘ የነበረው ቀጥተኛ የሆነ ሀላፊነት ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ & የጊዜ ብሎም የአቅም ጫና ሲያሳድርበት ቆይቷል::

## ለ. የነባሩ የዘር ግብይት ስርዓት ዋና ዋና ተግዳሮቶች

- ዘር በጥራት ፣ በዓይነት፣ በወቅቱ እና በበቂ መጠን ያለመድረስ እና በወቅቱ ያለማሰራጨት
- ዘር ለማግኘት ረጅም የግብይት ሰንሰለት መኖር
- በወረዳ ግብርና ባለሙያዎች እና ልማት ጣብያ ሰራተኞች የስራ ጫና ማስከተል እና የገንዘብ ጉድለት መከሰት
- የዘር መክረም እና ብክነት መኖር
- በመንግስት በጀት ላይ ጫና ማሳደር
- የአጋር አካላት ድርሻቸውን ወስደው ያለመተግበር
- የዘር አምራች ድርጅቶች በመንግስት ጥገኝነት ማሳደሩ
- ተጠያቂነት አለመኖር
- የዘር መረጃ በተገቢው ወቅትና ባግባቡ ለአርሶ አደሩ ያለመድረስ
- የዘር ጥራት ተቆጣጣሪው አካል በዘር ግብይት ወቅት የዘር ጥራት ቁጥጥሩን በባለቤትነት አለመስራት

## ሐ. መልካም አጋጣሚዎችና ስልታዊ መፍትሄዎች

- ምቹ የሆነ የዘር ህግ እና ስልት መኖር
- መንግስት የቀጥታ ዘር ግብይት እንዲስፋፋ ምቹ ሁኔታ መፍጠሩ
- የዘር አምራች ድርጅቶች ቁጥራቸው እየጨመረ መምጣትና አጋር አካላት መኖራቸው
- በሁሉም አካላት የቀጥታ ዘር ግብይት የተደገፈና ፍላጎት መኖር
- በአርሶ አደሩ የምርጥ ዘር በአይነትና በመጠን የመጠቀም ፍላጎቱ እያደገ መምጣቱ እና ምቹ የኤክስቴንሽን ስርአት መኖሩ
- የዘር ሽያጭ ወኪሎች በዘር ግብይት ላይ ለመሳተፍ ፍላጎት እያደገ መምጣት

# 2. የቀጥታ የዘር ግብይት ለምን አስፈለገ ?

በነባሩ የዘር ግብይት ስርአት ላይ የታዩ ተግዳሮቾችን በመቅረፍ የምርጥ ዘርን በጥራት ፣ በዓይነት፣ በመጠን፣ በወቅቱ ፣በተመጣጣኝ ዋጋ እና ተደራሽ በሆነ ቦታ እንዲሁም ተጠያቂነትና ባለቤትነት ሊኖር በሚያስችል ሁኔታ ለተጠቃሚው እንዲደርስ ለማስቻል::

## ሀ. የቀጥታ የዘር ግብይት እና ተያያዥ ቃላት ትርጓሜ

**የቀጥታ ዘር ግብይት** ማለት የዘር አምራች ድርጅቶች ዘርን በማምረት እና በማዘጋጀት በቀጥታ በራሱ መስመር ወይም በሚወክላቸው አካላት ወይም የግብርና ግብአት ነጋዴአማካይነት ዘርን ለተጠቃሚው ሃላፊነትን ወስዶ በተጠያቂነት መሸጥ ማለት ነው::

**የዘር ሽያጭ ወኪል** ማለት ግለሰብ ወይም ማህበራት ሆኖ የዘር አምራች ድርጅት ያመረተውን ዘር ለመሸጥ የሚያበቃውን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በመያዝ ከዘር አምራቹ ጋር በሚፈጽመው የውል ስምምነት መሰረት ለተጠቃሚው በውክልና የሚሸጥ አካል ማለት ነው::

የግብርና ግብአት ነጋዴ ማለት ድርጅት ወይም ግለሰብ ወይም ማህበራት ዘር እና ሌሎች የግብርና ግብአቶች ለመሸጥ የሚያበቃቸውን የብቃት ማረጋገጫ ሰርትፍኬት እና ፈቃድ ኖሮት በራሱ አቅም የግብርና ግብአቶችን ገዝቶ በማምጣት ለተጠቃሚው በቀጥታ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ በስሩ ቅርንጫፍ መደብር/ወኪል በመክፈት የሚሸጥ ፡፡

## ለ. የቀጥታ የዘር ግብይት ስርአት ዋና ዋና አላማዎች

- ተጠቃሚው ዘር በጥራት ፣ በዓይነት፣ በመጠን፣ በወቅቱ ፣ ተደራሽ በሆነ ቦታ እና በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኝ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ፤
- የዘር አምራች ድርጅቶች በቀጥታ ዘርን በተጠያቂነት እና በባለቤትነት ለተጠቃሚው ማድረስ
- የምርጥ ዘር ፍላጎትና አቅርቦት በማጣጣም የዘር መክረምን ወይም እጥረትን መቀነስ
- ከዘር ግዥ ፣ሽያጭ እና ስርጭት በተያያዘ በመንግስት በኩል የሚወጣን የበጀት ጫና መቀነስ ብሎም ማስቀረት
- ግብርና ባለሙያዎች እና የልማት ጣቢያ ሰራተኞችን የስራ ጫና በመቀነስ ሙሉ ጊዜያቸውን በኤክስቴንሽን የልማት ስራዎች ላይ እንዲያተኩሩ ማድረግ

## ሐ. የቀጥታ የዘር ግብይት ስርአት መርሆዎች

| መርሆ | ማብራሪያ |
|---|---|
| አማራጭ የግብይት መንገዶችን መጠቀም | የምርጥ ዘር አምራች ድርጅቶች በተለያዩ የዘር ግብይት ማሰራጫ መንገዶችን መምረጥ ይችላሉ (የግል ወኪል፣ የግብርና ግብአት ነጋዴ ፣ የህብረት ስራ ማህበራት እና በድርጅቱ የሽያጭ ሰራተኞች )<br>▪ ተወዳዳሪ የሆኑ የዘር አምራች ድርጅቶች በቀጥተኛ የዘር ግብይት ተጠቃሚ ወረዳዎች መኖርና አማራጭ ዝርያዎችን ማቅረብ<br>▪ ከአንድ በላይ አምራች ድርጅቶች በሌሉነት ሁኔታ አንድ አምራች ብቻ ያለውን ዘር ይዞ በሚፈልገው የመሸጫ መንገዶች በመምረጥ ዘር መሸኘ ይችላል |
| ገበያዉን መሰረት ያደረገ ዋጋ ትመና | ▪ የምርጥ ዘር አምራቹ በቀጥተኛ የዘር ግብይት ተጠቃሚ ወረዳዎች የዘር ዋጋን ነጻ ሆኖ በራሱ እንዲወስን እድል መስጠት |
| ለዘር ግብይት የምርጥ ዘር አምራቾች እና የዘር ሽያጭ ወኪሎች ቀጥተኛ ተጠያቂነትና ሃላፊነት ይወስዳሉ | ▪ የዘር ሽያጭ በአምራች ድርጅቱ ወይም በወኪል የሚከናወን ከሆነ የዘር መክረምን እና የጥራት መጓደልን የዘር አምራቹ ሃላፊነት ይወስዳል<br>▪ የዘር አምራች ድርጅቶች ለወኪሎቻቸው የኮሚሽን መጠንን መወሰንና መክፈል ይጠበቅባቸዋል<br>▪ የዘር ሽያጭ ወኪሎች የዘር ሽያጭ ተግባር የሚፈጽሙ ከሆነ የዘር መክረምን እና የጥራት መጓደልን ሃላፊነት ይወስዳሉ |
| ወኪሎችን የመምረጥና ማረጋጋጫ ሰርተፊኬት | ▪ የዘር ሽያጭ ወኪሎች የሚመረጡት በአምራች ድርጅቶች በኩል ነው<br>▪ የዘር ሽያጭ ወኪሎች በመምረጫ መስፈርቱ መሰረት በጥራት ተቆጣጣሪው ባለስልጣን ተገምግመው የብቃት ማረጋገጫ ሰርትፊኬት ይሰጣል<br>▪ በጥራት ተቆጣጣሪ ባለስልጣኑ ለሻጭ ወኪሎች የሚሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ሰርትፊኬት ለቋሚ በየአመቱ የሚታደስ እና በግዜያዊነት የሚሰጠው ደግሞ በባለስልጣኑ ቅርብ ክትትል ለአንድ የዘር ወቅት ብቻ የሚያገለግል ይሆናል |
| ወቅታዊ የዘር ግብይት መረጃ መያዝ እና ሪፖርት ማድረግ | ▪ የዘር አምራች ድርጅቶች እና የሽያጭ ወኪሎች የዘር ግብይት መረጃን ባግባቡ መያዝና ለሚመለከተው አካል ወቅታዊ ሪፖርት ማድረግ<br>▪ በየደረጃው ያሉ የግብርና ተቋማት የግብይት መረጃ መያዝና ለሚመለከታው አካል ወቅታዊ ሪፖርት ማድረግ |
| ሌሎች ለዘር ግብይቱ አጋዥ የሆኑ ሁኔታዎችን ማመቻቸት | ▪ ለግብአት መግዣ የብድር አገልግሎት ማመቻቸት<br>▪ ዘመናዊ የመረጃ መለዋወጫ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የዘር ዝውውርን መቆጣጠርና መከታተል |
| የግብይት ስርአቱን መደገፍ እና ማስተባበር | ▪ የግብርና ሚኒስቴር እና የግብርና ቢሮዎች ስራ ድርሻ ማስተባበርና ቁጥጥር ማድረግ ሲሆን ተወዳዳሪና ነጻ ገበያ ስርአት እንዲኖር ያበረታታል<br>▪ አጋር አካላት የግብይት ስርአቱን በአቅም ግንባታ ይደግፋሉ |
| በቀጥተኛ የዘር ግብይት ተጠቃሚ ወረዳዎች የተለያዩ የሰብል ዘሮች አቅርቦት | ▪ ዘር አምራች አካላት ከድቃይ በቆሎ በተጨማሪ ሌሎች ድቃይ ያልሆኑ ሰብል ዘሮችን ማምረትና ለተጠቃሚው በሽያጭ ማቅረብ |

## መ. የቀጥታ የዘር ግብይት ዋና ዋና ፋይዳዎች

- ምርጥ ዘር በጥራት፣ በዓይነት ፣ በመጠን፣ በጊዜ ፣በተመጣጣኝ ዋጋ እና ተደራሽ በሆነ ቦታ እንዲቀርብ አድርጓል
- የአርሶ አደሩን ትክክለኛ ፍላጎት እቅድ ማወቅ ማስቻሉ
- የዘር ግብይት ሰንሰለትን ማሳጠሩ
- ተጠያቂነትና ሃላፊነት እንዲኖር አድርጓል
- የአርሶ/ከፊል አርብቶ አደሩን ጊዜ፣ ጉልበት እና ገንዘብ መቆጠቡ
- ጥራት ያለው ዘር ፣ አማራጭ ዝርያዎችና አቅራቢ ድርጅቶች እንዲኖሩ አድርጓል
- የዘር መሸጫ ሱቅ በዘር ሽያጭ ወቅት በሳምንቱ ሙሉ ቀን ክፍት ሆኖ መገኘቱ ለተጠቃሚዎች የዘር ተደራሽነትን አሳድጓል
- የዘር አምራቾችና ሻጭ ወኪሎችን ተነሳሽነትን እና የውድድር መንፈስን አሳድጿል
- የዘር አምራች ድርጅቶች በተለያዩ መጠን ዘርን አሽጎ በማቅረብ የተጠቃሚዎችንና የደንበኞችን ፍላጎት ማርካት አስችሏል
- የግብርና ባለሙያዎች እና ልማት ሰራተኞች ስራ ጫና ቀንሷል
- የዘር ማደር ሁኔታን መቀነሱ ብሎም ማስቀረቱ ከዚህም ጋር ተያይዞ የሚወጣን የመንግስትን ወጪ አስቀርቷል
- በምርጥ ዘር አቅርቦት እና ስርጭት ተያይዞ የሚወጡ የመንግስት መጪዎችን ቀንሷል
- የአርሶ/ከፊል አርብቶ አደሩ የምርጥ ዘር ፍላጎትና አጠቃቀም ጨምሯል
- ከምርጥ ዘር የቀጥታ ሽያጭ ጋር በተያያዘ የስራ እድል መፈጠርና ብሎም ትርጉም ባለው መልኩ ገቢ መጨመር
- ምርትና ምርታማነትን በመጨመር የአርሶ/ከፊል አርብቶ አደሩ ገቢ እንዲጨምር አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

## ሠ. ያጋጠሙ የአፈጻጸም ተግዳሮቶችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች

| ተ/ቁ | ተግዳሮት | የመፍትሄ ሀሳቦች |
|---|---|---|
| 1 | የወረዳ ባሙያዎች እና የልማት ጣብያ ሰራተኞች ዘር መግዣ ገንዘብ ማሰባሰብ እና ዘር ማጓጓዝ ተግር ላይ መሳተፋቸው በመደበኛው የኤክስቴንሽን ስራ ላይ ጫና አሳድሮል | የወረዳ ባለሙያዎች እና የጣቢያ ሰራተኞች በዋነኛነት ለዘር ሽያጭ ወኪሎች የቴክኒክ ድጋፍ መስጠትና ለአርሶአደሩ መደበኛውን የኤክስቴንሽን ስራ ማከናወን |
| 2 | ደረጃውን የጠበቀ መጋዘን ያለመኖር እና የመጋዘን እጥረት | በሁሉም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ መጋዘን አገልግሎት እንዲሟላ ማድረግ |
| 3 | የዘር አምራች ድርጅቶች በቁጥርና በአቅም ውስን መሆን | ምቹ ሁኔታን በመፍጥር የዘር አምራች ድርጅቶችን በቁጥር እና በአቅም እንዲጎለብቱ ማድረግ |
| 4 | የዘር መሸጫ ጣቢያዎች ተደራሽ ያለመሆን | የዘር መሸጫ ጣቢያዎች ለተጠቃሚውተደራሽ ለማድረግ ወኪሎችንና ጣቢያዎችን ማብዛት |
| 5 | የዘር ጥራት ቁጥጥር አካል መስፈርቱን አሞልተው ለሚገኙ የሽያጭ ወኪሎች በወቅቱ የብቃት ማረጋገጫ አለመሰጠት | የዘር ጥራት ቁጥጥር አካላትን አቅም በመገንባት ለሽያጭ ወኪሎች በወቅቱ የብቃት ማረጋገጫ እንዲስጥ ማስቻል |
| 6 | በአንዳንድ የቀጥታ የዘር ግብይት ተጠቃሚ ወረዳዎች ውስጥ ጎን ለጎን የተምዷዊ የዘር ግብይት ስራ ማካሄድ | የቀጥታ የዘር ግብይት በሚካሄድባቸው ወረዳዎች ውስጥ ወጥ የሆነ የቀጥታ ዘር ግብይት ብቻ እንዲካሄድ ጥረት ማድረግ |
| 7 | የዘር አምራቾች የገበያ ጥናት እና የዘር ማስተዋወቅ ስራን በበቂ ሁኔታ ያለማካሄድ | ዘር አምራቾች የገበያ ጥናት በማድረግ የተጠቃሚን ፍላጎት ማወቅ እንዲሁም ምርታቸውን ለመሸጥ ዘር ማስተዋወቅ ስራ እንዲሰሩ ማበረታት |
| 8 | የዘር አምራች ድርጅቶች ህብረት ስራ ማህበራት ላይ ብቻ ጥገኛ መሆን አማራጭ የግብይት ሰንሰለትን አለመጠቀም | የዘር አምራች ድርጅቶች የተለያዩ የዘር ሽያጭ ወኪሎችን(ማህበራተን; የግልና የግብርና ግብአት ነጋዴዎችን) እንዲጠቀሙ ማበረታታት |
| 9 | የዘር አምራች ድርጅቶች የራሳቸውን ወኪል በወቅቱ ያለመምረጥና ለተቆጣጣሪዉ አካል ያለማሳወቅ | የዘር አምራች ድርጅቶች የሚወክሏቸውን ወኪሎች በራሳቸው አቅምና በወቅቱ መምረጥና ለሚመለከተው አካል መምረጥና ማሳወቅ |
| 10 | የባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ክፍተትና የአቅም ውስንነት ያለመናበብ መኖር | የባለድርሻ አካላትን ስለ ቀጥተኛ ዘር ግብይት በተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ወርክሾፖችና ስልጠናዎች ግንዛቤን ማሳደግ |

## 3. የቀጥታ ዘር ግብይት ሂደት

**3. 1.** የአፈጻጸም ግምገማ:-የባለፈውን አመት የቀጥታ ዘር ግብይት ስርዓትን አጠቃላይ አፈጻጸም በመገምገም የቀጣዩን አመት እቅድ ውይይት በማድረግ የስራቱን ቀጣይ አቅጣጫ የሚቀመጥበት ሂደት ነው

**3.2.** የወረዳዎች ልየታ:-የቀጥታ ዘር ግብይት ስርዓትን ለማስፋፋት በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የሚመለከታቸው አካላት ወርዳዎችን ይመለምላሉ። የመመልመያ መስፈርቱም:-

- ኩታ ገጠም የሆኑ ወረዳዎች
- የወረዳዎቹ የሰብል ምርታማነት
- ለክትትል ያለው አመቺነት
- በዘር አምራቾች እጅ የሚገኘው የዘር አይነትና መጠን
- የዘር አምራች ድርጅቶች ፍላጎት

**3.3.** የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት:-የዘር አምራች ድርጅቶች የወረዳውን አጥቃላይ የዘር ፍላጎት የዳሰሳ ጥናት ያደርጋሉ

**3.4.** የሽያጭ ጣቢያዎችን መለየት:-የዘር አምራች ድርጅቶች በመረጡት ወርዳ በመገኘት የሽያጭ ጣቢያዎችን ተደራሽና አማካይ በሆነ ቦታ ላይ ይመረጣሉ

**3.5.** የሽያጭ ወኪሎች መረጣ ግምገማ እና እውቅና አሰጣጥ:- የዘር አምራች ድርጅቶች በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የራሳቸውን የዘር ሽያጭ ወኪል በመመልመል ለዘር ቁጥጥር ባለስልጣን ካሳወቁ በኋላ የባለስልጣን መስሪያቤቱ አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታ መሟላቱን በማረጋገጥ እውቅና ይሰጣል የዘር አምራች ድርጅቶችም እውቅና ከተሰጣቸው የሽያጭ ወኪሎች ጋር ውል ስምምንት ይፈራረማሉ::

## 4. የባለድርሻ አካለት የስራ ድርሻና ሃላፊነት

### ሀ. የዘር አምራች ድርጅት

- የዘር ፍላጎት የዳሰሳ ጥናት ያደርጋሉ፣
- ጥራቱን የጠበቀ ምርጥ ዘር ያመርታሉ፣
- በቀጥታ የዘር ግብይት የሚሳተፍበትን ወረዳ እና የሚያቀርበውን ዝርያ ዓይነትና መጠን ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፣
- የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ምርታቸውን ለተጠቃሚው ያስተዋውቃል፣
- የሽያጭ ወኪል/ዲለር በመምረጥ ለጥራት ተቆጣጣሪው አካል በተቀመጠው የግዜ ሰሌዳ ያሳውቃል፣
- በጥራት ተቆጣጣሪው አካል እውቅና ካገኙ የሽያጭ ወኪሎች ጋር ብቻ ውል ይገባል፣
- ምርቱን በቀጥታ ወይም በወኪሎቻቸው አመካይነት ለተጠቃሚው ይሸጣል፣
- ለሽያጭ ወኪሎቻቸው የኮሚሽን ክፍያ በውሉ መሰረት ይፈጽማል፣
- የዘር ግብይት ሂደቱን በመጋዘንና በመስክ በመከታተል መረጃ መያዝና ግብረ መልስ መቀበል፣
- ከዘር ጥራት ጋር በተየያዘ ከተጠቃሚው ለሚነሱ ችግሮች ከሚመለከተው አካል ማረጋገጫ ሲገኝ ሀላፊነት እና ተጠያቂነትን ይወስዳል፣
- ከጥራት ጋር በተየያዘ ለሚከሰቱ ችግሮች ከሽያጭ ወኪላቸው ጋር በገቡት የውል ስምምነት መሰረት ሀላፊነት ይወስዳል፣
- የዘር ወቅት እንዳለፈ ሳይሸጥ የቀረን ዘር ከወኪሎቻቸው ጋር በገቡት የውል ስምምነት መሰረት ያነሳሉ

### ለ. የሽያጭ ወኪል

- የዘር ሽያጭ ወኪልነትን/የዲለርነት መስፈርቶች አሟልቶ መገኘት (ዕዝል 1)፣
- በአምራቹ የሚቀርበው ዝርያ በጥራት ተቆጣጣሪው አካል ህጋዊ ማረጋገጫ የተሰጠው መሆኑን ማወቅ፣
- በአካባቢው የሚፈለገውን ምርጥ ዘር በመጠንና በአይነት መለየት፣
- ከምርጥ ዘር እምራቾች ጋር የሽያጭ ውል መዋዋል፣
- የዘር ሻጭ ወኪሉ የመሸጫ ጣቢያውን ሁልጊዜ ክፍት በማድረግ የዘር መሸጥ ስራውን ያከናውናል
- የሽያጭ መረጃ በተጠቃሚ በስም ዝርዝር ይይዛል ለሚመለከተው አካልም ይሰጣል
- በጥንቃቄ እና በአያያዝ ችግር በሚከሰት የዘር ጥራት መጓደል ውልን መሰረት በማድረግ ተጠያቂ ይሆናል
- የዘር ሽያጭ ወኪሉ እራሱ ባሳተመው ወይም ከዘር አምራች ድርጅቱ ባገኘው ደረሰኝ መሰረት መሸጥ ይኖርበታል፣
- ለተጠቃሚው ተገቢውን ምክር ይሰጣል፣
- የሚሸጠውን ምርጥ ዘር የሚወክል አንድ የናሙና ከረጢት ከፍቶ ለተጠቃሚው ማሳየት፣
- የሚሸጠውን ምርጥ ዘር ማስተዋወቅ፣
- በድህረ ሽያጭ ጊዜ የአርሶ አደሩን ማሳ በመጎብኘት፣ ምክር ማስጠትና ግብረ መልስ ለአምራቹ መስጠት፣

## ሐ. የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ተቋም (ፌዴራል እና ክልል)

የግብርና ግብአት ጥራት ቁጥጥር ዘርን በተመለከተ ቁጥጥርን ለማካሄድና ለማረጋገጥ የተቋቋመ ተቋም እንደመሆኑ የሚከተሉት የስራ ድርሻዎች ይኖሩታል፡-

- በዘር ጥራትና ቁጥጥር ዙርያ ያሉትን የህግ ማዕቀፎችና አሰራሮችን ለሚመለከታቸው አካላት የግንዛቤ ማሰጨበጫ እና ስልጠና ይሰጣል
- ለዘር አምራቾች ዘር የማምረት፣ የማቀነባበርና የማከፋፈል የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ፍቃድ ይሰጣል፣
- የዘር ጥራት ቁጥጥርን በየደረጃው በማካሄድ ሰርቲፊኬት ይሰጣል፣ከአሰራር ውጭ የሆነን አካል ፍቃዱን ይነጥቃል
- በዘር ሽያጭ ላይ የሚሳተፉ ወኪሎችን በመስፈርቱ መሰረትየብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ፍቃድ ይሰጣል፣
- በዘር ሽያጭ ጣቢያዎች በመገኘት የጥራት ቁጥጥርና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣
- ከዘር ሽያጭ በኋላ የመስክ ቁጥጥር እና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣

## መ. ግብርና ሚኒስቴር

- የቀጥታ ዘር ግብይትን በተመለከተ አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችንና የአፈፃፀም መመሪያዎች ያወጣል መፈፀማቸውንም ይከታተላል፣
- በቀጥታ ዘር ግብይት አፈፃፀም ላይ የሚታዩ የአሰራር ክፈተቶችን በመለየት የአቅም ግንባታ ስራዎች ያከናውናል፣
- የቀጥታ ዘር ግብይትን አፈፃፀም ከክልል ግብርና ቢሮዎችና ከሌሎች አጋር ኣካላት ጋር በመሆን ይገመግማል፣ የማስተካከያ ሃሳቦች ይሰጣል፣ መፈፀማቸውንም ይከታተላል፣
- የቀጥታ የዘር ግብይት እንዲስፋፋና ተቋማዊ እንዲሆን ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል

## ሠ. የክልል ግብርና ቢሮ

- በክልሉ የሚገኙ የዘርፉ ባለ ድርሻ አካላትን ያስተባብራል፤
- የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ለዘር አምራቾች፤ ለወኪሎቻቸውና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት ይሰጣል፤
- ከቀጥታ ዘር ግብይትጋር በተገናኘ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ይሰጣል፤
- ስለ ቀጥታ ዘር ግብይት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ይሰራል፤
- ወቅታዊ የዘር ገበያ መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት ይሰጣል፤
- የብድር አገልግሎት ያመቻቻል፤
- መልካም ተሞክሮዎችን ይቀምራል ተደራሽ እንዲሆኑም ያደርጋል፤
- ቀጣይነት ያለው ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤
- የቀጥታ ዘር ግብይትን አፈፃፀም ከዞን እና ከወረዳ ግብርና ቢሮዎችና ከሌሎች አጋር ኣካላት ጋር በመሆን ይገመግማል፣ የማስተካከያ ሃሳቦች ይሰጣል፣ መፈፀማቸውንም ይከታተላል፣
- የቀጥታ የዘር ግብይት እንዲስፋፋና ተቋማዊ እንዲሆን ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል
- የስራ መመሪያዎች ለተለያዩ አካለት ያደርሳል

## ረ. የሕብረት ስራ ማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ቢሮ/ኤጀንሲ/ፅ/ቤት

- በሽያጭ ወኪልነት እና በዘር አምራችነት ለሚሰሩ ህብረት ስራ ማህበራት የአቅም ግንባታ ስራ ይሰራል፤
- በዘር ብዜት ለሚሳተፉ ማህበራት ወደ ቀጥታ ዘር ግብይት ስርአት እንዲገቡ ድጋፍ ያደርጋል፤
- ወቅታዊ የዘር ገበያ መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት ይሰጣል፤
- ተገቢ የመዝገብ፣ የፋይናንስ አያያዝና አስተዳደር ድጋፍ ያደርጋል፣
- የአባላት ተሳትፎ እነዲኖር የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ይሰራል፣
- የህግ ምክርና የኦዲት አገልግሎት ይሰጣል፤
- የብድር አገልግሎት ያመቻቻል፤

## ሰ. የክልል የዘር አብይ ኮሚቴ

- የቀጥታ ዘር ግብይት አፈፃፃም አቅጣጫ ይሰጣል
- ዘር አምራቾች የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ያግዛል
- የቀጥታ ዘር ግብይት አፈፃፃም ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ የማስተካከየ ሃሳብ ያስቀምጣል
- ዘር አባዥ ድርጅቶችን አቅም ለማሳደግ አስፈላጊውን ምቹ ሁኔታ ያመቻቻል
- የቀጥታ የዘር ግብይት እንዲስፋፋና ተቋማዊ እንዲሆን ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል

## ሸ. የዞን ግብርና መምሪያ

- በዞኑ የሚገኙ የዘርፉ ባለ ድርሻ አካላትን ያስተባብራል፤
- የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ለዘር አምራቾች፤ ለወኪሎቻቸውና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት ይሰጣል፤
- ከቀጥታ ዘር ግብይትጋር በተገናኘ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ይሰጣል፤
- ስለ ቀጥታ ዘር ግብይት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ይሰራል፤
- ወቅታዊ የዘር ገበያ መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት ይሰጣል፤
- የብድር አገልግሎት ያመቻቻል፤

- መልካም ተሞክሮዎችን ይቀምራል ተደራሽ እንዲሆኑም ያደርጋል፤
- ቀጣይነት ያለው ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤
- የቀጥታ ዘር ግብይትን አፈፃፀም ከወረዳ እና ከቀበሌ ግብርና ጽ/ቤትዎችና ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በመሆን ይገመግማል፣ የማስተካከያ ሃሳቦች ይሰጣል፣ መፈፀማቸውንም ይከታተላል፣
- የቀጥታ የዘር ግብይት እንዲስፋፋና ተቋማዊ እንዲሆን ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል
- ከክልል የሚላኩለትን የስራ መመሪያዎች ለተለያዩ አካለት ያደርሳል
- በገበያ ፍላጎት ጥናት ላይ ድጋፍ ያደርጋል፤
- የዘር እጥረት ሲያጋጥም ከአምራች ድርጅቶች ጋር  በመነጋገር የዘር ሽግሽግ እንዲያደርጉ ያሳውቃል እና ይከታተላል፣
- ከፋይናንስ ተቋማት ጋር በመሆን የብድር አገልግሎት ያመቻቻሉ፤
- ቀጣይነት ያለው የክትትል እና ድጋፍ ያደርጋል፤

## ቀ.  የወረዳ ግብርና ጽ/ቤት

- የቀጥታ ዘር ሽያጭ ሂደት አግባቡን ጠብቆ እንዲጎንዝ ለሁሉም የባለድርሻ አካላት የስርጸት ስራን ይሰራል
- በምርጥ ዘር አምራቾች እና በሽያጭ ወኪሎች መሀከል በአማካይነት ይሰራል
- ለዘር ሽያጭ ወኪሎች ምቹ ሁኔታን  በማስተዋወቅ እና የአቅም ግንባታን በማድረግ ይሰራል
- ያገጠሙ ችግሮችን በመከታተል ለዞንና ለክልል ግ/ቢሮ በወቅቱ ሪፖርት ያቀርባል
- ለዘር ሽያጭ ወኪሎች የሙያ ድጋፍ ያደርጋል
- የሽያጭ ጣቢያዎች እና መጋዘኖች ጥራታቸውን የጥበቁ እዲሆኑ ሞያዊ እገዛ ያደርጋል
- ለአርሶ አደሩ ስለቀጥታ ዘር ሽያጭ አካሄድ እና መርህ ያስተምራል
- አራሶ አደሩ የመረጠውን ዘር በአግባቡ እንዲጠቀም ያስተምራሉ፣ ያሳውቃል
- ያገጠሙ ችግሮችን በመከታተል ለወረዳ ግ/ቢሮ ወይም አመራር በወቅቱ ሪፖርት ያቀርባል

## በ. የቀበሌ ግብርና የልማት ጽ/ቤት

- በቀጥታ ዘር ሽያጭ ስርዓት በኩል ስለሚከናወን የዘር ግበይት ሂደት ለአርሶ አደሩ ተገቢዎን መረጃ ይሰጣል
- ለተጠቃሚው የተመረጡ የዘር የሽያጭ ማእከላትን እና የሽያጭ ወኪሎችን ማሳወቅ
- ለተጠቃሚው የዘር አቅራቢ ድርጅቶችንና የሚያቀርቡትን  የዘር ዓይነት በዝርያ  ማሳወቅ
- አርሶ አደሩ የመረጠውን ዘር በአግባቡ እንዲጠቀም ያስተምራሉ ያሳውቃሉ
- አጠቃላይ መረጃዎችን ከተለያዩ አካላት (ዘር አቅራቢ ድርጅቶች፣ የግል ወኪሎች፣ አርሶ አደሩ) በመሰብሰብ ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል
- የቀበሌወ የዘር ፈላጎት መረጃ መሰብሰብ ማጠናከርና ሪፓርት ያደርጋል
- ያገጠሙ ችግሮችን በመከታተል ለወረዳ ግ/ቢሮ በወቅቱ ሪፖርት ያቀርባሉ

## ተ. የልማት አጋር  አካል

- በየደረጃው ለሚገኙ የዘርፍ ባለድረሻ አካላት የአቅም ግንባታና በበጀት ድጋፍ ያደርጋል
- መልካም ተመክሮዎች እንዲቀመሩና ተደራሽ እንዲሆኑ ያግዛል

## ቸ.  አርሶ አደር

- የእርሻ ማሳውን በአግባቡ ማዘጋጅት
- የሚሰጠውን የሙያ ምክር መሰረት አድርጎ የሚፈልገውን ግብአት መጠየቅና መጠቀም
- ዘር ለመሸጥ ፍቃድ የተሰጣቸውን የዘር አምራች ድርጅት፣  የሽያጭ ጣቢያዎች እና የሽያጭ ወኪሎች ለይቶ ማወቅ
- የሚገዛውን የዘር አይነት ናሙና በሽያጭ ጣቢያ በማየት ይገዛል
- የዘር ከረጢቱ ማሸጊያ ያልተፈታ እና 'ታጉ' ያልተነቀለና የአምራቹ ስምና መለያ ምልክት መሆኑን ማረጋገጥ
- በከረጢቱ ውጭና ውስጥ የሚገኘውን የጥራት ማረጋገጫ ታግ በአግባቡ ማስቀምጥ
- ከዘር ጥራት መጓደል ተያይዞ የሚከሰት ችግር ካጋጠመው በቀበሌው ውስጥ ለሚገኝ የልማት ጣቢያ ሰራትኛ ማሳወቅ እና ካሳ መጠየቅ፣

# 5. የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ

## ሀ. ዋና የአፈጻጸም ጠቋሚ መለኪያዎች

1.የአርሶ አደሩ እርካታ፣

- ○ በጥራት፣ በጊዜ፣ በመጠን፣ በዋጋ፣ በአቅርቦት ቦታ፣ የተጠያቂነት ስርዓት መኖር

2. የዘር አቅራቢ ድርጅት ውጤታማነት ‘

- ፍላጎት፣ አቅርቦት፣ ሽያጭ፣ የከረመ ዘር መጠን፣ ዋጋና የተገኘ ትርፍ
- ተጨማሪ የዘር ፍላጎት መፍጠር

3. የመንግስትን የዘር ስርዓት ልማት ስትራተጂ

- የዘር አጠቃቃም ሽፋን መጨመር
- የስራ ዕድል መፍጠር
- በዘር ፍላጎትና አቅርቦት መካካል ያለው ልዩነት ማጥበብ
- የመንግስት ከዘር አቅርቦትና ስርጭት ጋር በተያያዘ ያለውን የስራ ጫናና ወጭ መቀነስ ብሎም ማስቀረት

## ለ. የክትትልና የግምገማ ግንኙነት ሂደቶች

- ዋና ዋና የአፈጻጸም ጠቋሚ መለኪያ ሰንጠረዥ በየሁለት ሳምንቱ (በ15ኛውና በ30ኛው ቀን) የቀበሌ የልማት ሰራተኛ ተሞልተው ለወረዳ ግበርና ፅ/ቤት ሪፓርት ያደርጋሉ ፣
- የወረዳው የቀጥታ ዘር ግብይት ተጠሪ የየቀበሌው መረጃ አጠናቅሮ በየሁለት ሳምንቱ (በ17ኛውና በ2ኛው ቀን) ለክልሉ ግብርና ቢሮ ሪፓርት ያደርጋል፡፡
- የክልሉ ግብርና ቢሮ የቀረበውን ሪፓርት መሰረት አድርጎ ከዘር አብይ ኮምቴ ጋር አፈፃፀሙን በመገምገም ግብረመልስ ለወረዳዎች ይልካል፡፡
- አጠቃላይ ዓመታዊ የቀጥታ ዘር ግብይት ሂደት በመገምግም ቀጠይ አቅጣጫዎች ያስቀምጣል

ቅፅ 1. የአቅርቦትና ስርጭት መጠን

| ቁጥር | ሰብል | ዝርያ | የዘር አቅራቢ ስም | ፍላጎት (በኩንታል) | አቅርቦት | የከረመ ዘር ብዛት (በኩንታል) | ነጠላ የመሸጫ ዋጋ | ዘር የገዙ የቤተሰብ አስተዳዳሪዎች | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | ወንድ | ሴት |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |

ቅፅ 2. የዘር ጥራት

| ቁጥር | ሰብል | ዝርያ | አቅራቢ | የጥራት ችግሩ ዓይነት | የጥራት ችግር ሪፓርት ያደረጉ አርሶ አደሮች ብዛት | የጥራት ችግር የሸፈነው አከባቢ (በሄክታር) | የተመስከረለት ዘር ተጠቃሚ አርሶ አደሮች ብዛት | የጉዳት መጠን በፐርሰንት | የተወሰደው እርምጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |

የችግሩ ዓይነት፣ 
- የብቅለት ችግር ያለበት
- በበሽታ የተጠቃ (በተባይ በነቀዝ)
- የአካል ጉድለት ያለበት ዘር (ደቃቅ፣ የተጨማደደ፣ የተሰባበረ)

ቅፅ 3. የዘር ስርጭት ወቅት

| ቁጥር | ሰብል | ዝርያ | የዘር አቅራቢ ስም | በወረዳው ዘር ለመዝራት የሚመች ግዜ ( ግንበት 4ኛ ሳምንት) | በወረዳው ዘር የተሰራጨበት ጊዜ ( ግንበት 2ኛ ሳምንት) |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |

ቅፅ 4- የዘር አቅራቢ ድርጅቶች የዘር ስርጭት ሂደት

| ቁጥር | ሰብል | ዝርያ | የዘር አምራች | የዘር ሸያጭ ወኪል ዓይነትና ብዛት | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የግል | | | ሕስማ | | | ዩኒየን | | | በአምራቹ መሸጫ ቦታ | | |
| | | | | ቁጥር | የተቀበለው መጠን (ኩንታል) | የተሸጠው መጠን (በኩንታል) | ቁጥር | የተቀበለው መጠን (በኩንታል) | የተሸጠው መጠን (በኩንታል) | ቁጥር | የተቀበለው መጠን (በኩንታል) | የተሸጠው መጠን (በኩንታል) | ቁጥር | የተቀበለው መጠን (ኩንታል) | የተሸጠው መጠን (በኩንታል) |
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | |

ቅፅ 5- ወረዳዎች ለዘር ስርጭት የሚያወጡት ወጭ ግምት

| ቁጥር | የወጭ ዓይነት | ዓመታዊ የወጭ ስሌት ግምት | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | ለትራንስፓርት | | |
| 2 | መጨኛ ማውረጃ | | |
| 3 | ለአበል | | |
| 4 | የመጋዘን ኪራይ | | |
| 5 | ሌላ ወጭ | | |

ቅፅ 6-የዘር ሽያጭ ተጠቃሚ ዝርዝር መረጃ መመዝገቢያ

| ተ.ቁ | የዘር ተጠቃሚ ሙሉ ስም | አድራሻ | | የዘር | | የተገዛ ዘር መጠን (በኪ.ግ) | ቀን (ግዥዉ የተከናወነበት) | ፊርማ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወረዳ | ቀበሌ | አይነት | ዝሪያ | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |

የዘር ሻጩ ስም፡-____________________ ቀን፡-________________ ፊረማ፡-____________________

ቅፅ 7- የዘር ሸያጭ ኤጀንት አመራረጥ መመዘኛ:- ለቀጥታ ዘር ሽያጭ የፓይለት ፕሮግራም ጊዜ ብቻ የሚያገለግል

| መመዘኛ | የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት | በዘር ላብራቶሪዊች የቅርብ ክትትል ደረጃ ለሚያዙ |
|---|---|---|
| መጋዘን | • መጋዝኑ በቂ የአየር ማስገቢያ መስኮት ያለው:: መስኮቱ በሜሽ ሽቦ የተዘጋ ሊሆን ይገባል:: ግድግዳው ከጭቃ ወይም በብሎኬት የተሰራ ሊሆን ይችላል:: መጋዝኑ ባጠቃላይ ለመጋዝንነት ተግባር የተሰራ ሊሆን ያስፈልጋል:<br>• ወለሉ ከኮንክሪት የተሠራ ሊሆን ይገባል::<br>• ዘሩ የሚቀመጥበት ፔሌት የተሰራለት ሊሆን ይገባል::<br>• ግድግዳው ዐይጥ የማይሰገባ ሆኖ የተሰራ<br>• ዘሩ ከማዳበሪያና ከጸረ ተባይ ኬሚካሎች ተለይቶ ሊከማች ይገባል::<br>• ዘሩ ሲከማች በሎት አደራደር መሰረት ሆኖ ሁለት ኢንተርፕራይዞች ባሉበት ዘሮቻቸውን በመጋዝኑ የተለያዩ ሥፍራዎች ለየብቻ ማስቀመጥ<br>• መጋዝኑ ባግባቡ ሊጸዳ ይገባል::<br>• የዘር ከረጢቶች ከግድግዳ ቢያንስ **50** ሳ. ሜ ርቀው መደርደር ይኖርባቸዋል::በሎቶች መካከል ቢያንስ የ75 ሳ.ሜ ክፍተት ለመንገድ ሊኖር ይገባል::<br>• በጣሪያውና በዘር ክምችቱ ጫፍ መካከል በቂ ክፍተት ሊኖር ይገባል::<br>• ባጠቃላይ አየር በመጋዝኑ ውስጥ በበቂ ሁኔታ ሊሸራሸር ይገባል::<br>• ኤጀንቱ መጋዝኑን በኪራይ፣በስጦታ ያገኘው ወይም የራሱ የሆነ ሊሆን ይችላል:: | • ጊዚያዊ የዘር ማከማቻው የራሱ የሆነ በስጦታ ወይም በኪራይ የተገኘ መኖርያ ቤት ሊሆን ይችላል::<br>• ወለሉ ከኮንክሪት የተሠራ ሊሆን ይገባል::<br>• ዘሩ የሚቀመጥበት ፔሌት የተሰራለት ሊሆን ይገባል::<br>• ግድግዳው ዐይጥ የማያስገባ ሆኖ የተሰራ<br>• ዘሩ ከማዳበሪያና ከጸረ ተባይ ኬሚካሎች ተለይቶ ሊከማች ይገባል::<br>• ዘሩ ሲከማች በሎት አደራደር መሰረት ሆኖ ሁለት ኢንተርፕራይዞች ባሉበት ዘሩ በአንድ ክፍል ለየብቻ መቀመጥ ይኖርበታል:: ማከማቻውም ለዚህ በቂ ሊሆን ይገባል<br>• መጋዝኑ ባግባቡ ሊጸዳ ይገባል::<br>• የዘር ከረጢቶች ከግድግዳ ቢያንስ **50** ሳ. ሜ ርቀው መደርደር ይኖርባቸዋል::በሎቶች መካከል ቢያንስ የ**75** ሳ.ሜ ክፍተት ለመንገድ ሊኖር ይገባል::<br>• በጣሪያውና በዘር ክምችቱ ጫፍ መካከል በቂ ክፍተት ሊኖር ይገባል::<br>• ባጠቃላይ አየር በጊዚያዊ ማከመቻው ውስጥ በበቂ ሁኔታ ሊሽራሽር ይገባል::<br>• ዘሩ ለአጭር ጊዜ ብቻ(ከአንድ ሳምንት ላልበለጠ ጊዜ) በጊዚያዊ ማከማቻው የሚቆይ ከሆነ |
| የትምህርት ሁኔታ | • ቢያንስ አስረኛ ክፍል ያጠናቀቀና የትምህርት ማስረጃ ማቅረብ የሚችል::<br>• እርሱ ያላጠናቀቀ ከሆነ ሌላ ሰው/ ዘመድ ወይም ልጅ ወይም ሌላ ተቀጣሪ/ በሻጭነት መቅጠር የሚችል<br>• ለማህበራት ሲሆን የማ/በሩ ተቀጣሪ የሽያጭ፡ የመጋዝን ወይም የሂሳብ ሰራተኛ እንደ ዘር ሻጭ ያገለግላል:: | • ቢያንስ አስረኛ ክፍል ያጠናቀቀና የትምህርት ማስረጃ ማቅረብ የሚችል ቢሆን ይመረጣል::<br>• **10**ኛ ክፍል ያጠናቀቀ ልጁን ወይም ሌላ ግልሰብ መቅጠር ከቻለም መልካም ነው::<br>• ካልሆነ ግን ከ **10**ኛ ክፍል በታች ሆኖም ፈጣን ተግባቢና በዘር አቅራቢው ድርጅት ተመራጭ ሆኖ ከተገኘም በክትትል ከሚታዩት ውስጥ ሊካተት ይችላል:: |
| ልምድ | • ቢቻል በዕጽዋት ዘርና ሌሎች ግብዓቶች ዘር ሽያጭ የስራ ልምድ ያለው/ላት:: ጡረታ የወጡ የግብርና ባለሙያዎች / በተለይም በግብርና ግብዓት/ ቅድሚያ ዕድል ይሰጣቸዋል:: | • ቢቻል በዕጽዋት ዘርና ሌሎች ግብዓቶች ዘር ሽያጭ የስራ ልምድ ያለው/ላት:: ጡረታ የወጡ የግብርና ባለሙያዎች /በተለይም በግብርና ግብዓት/ ቅድሚያ ዕድል ይሰጣቸዋል:: |
| ሥልጠና | • በመንግስታዊ ድርጅቶችም ሆነ በመ.ያ.ድ በግብርና ግብዓቶች በዋናነተም በዕጽዋት ዘር አያያዝና ሽያጭ ላይ ከዚህ በፊት በቂ ሥልጠና የወሰደና ማስረጃ ማቅረብ የሚችል<br>• ከላይ የተጠቀሰው ካላሟላ ግን ከዚህ በኋላ በሚዘጋጁ አጫጭር ሥልጠናዎች ለመካፈል ፈቃደኛ የሚሆንና የሚዘጋጅለትን መመዘኛ ፈተና ማለፍ የቻለ | • በመንግስታዊ ድርጅቶችም ሆነ በመ.ያ.ድ በግብርና ግብዓቶች በዋናነትም በዕጽዋት ዘር አያያዝና ሽያጭ ላይ ከዚህ በፊት በቂ ሥልጠና የወሰደና ማስረጃ ማቅረብ የሚችል<br>• ከዚህ በኋላ በሚዘጋጁ አጫጭር ሥልጠናዎች ለመካፈል ፈቃደኛ የሚሆንና የሚዘጋጅለትን መመዘኛ ፈተና ማለፍ የቻለ |
| ተግባቢነት | • የተሰጠውን ዘር በማስተዋወቅ ሽያጭን የሚያፋጥን በማ/ ሰቡ ዘንድ ተደማጭና ተግባቢነት ባሕርይ ያለው | • የተሰጠውን ዘር በማስተዋወቅ ሽያጭን የሚያፋጥን በማ/ሰቡ ዘንድ ተደማጭና ተግባቢነት ባሕርይ ያለው |
| ታማኝነት | • በማ/ሰቡ እምነት የሚጣልበት ስለመሆኑ ከወረዳው የምስክርነት ደብዳቤ ለአምራቹ ማቅረብ የሚችል:: | • በማ/ሰቡ እምነት የሚጣልበት ስለመሆኑ ከወረዳው የምስክርነት ደብዳቤ ለአምራቹ ማቅረብ የሚችል:: |
| ማስያዣ | • የግል ኤጀንት ከሆነ ከአምራቾች ለሚቀርብለት ዘር ዋጋ የሚመጥን ንብረት በመያዣነት ማቅረብ የሚችል | • የግል ኤጀንት ከሆነ ከአምራቾች ለሚቀርብለት ዘር ዋጋ የሚመጥን ንብረት በመያዣነት ማቅረብ የሚችል |